M10/1/A1AMH/SP2/AMH/TZ0/XX

22100016

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Friday 14 May 2010 (morning)
Vendredi 14 mai 2010 (matin)
Viernes 14 de mayo de 2010 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.

2210-0016
3 pages/páginas
© International Baccalaureate Organization 2010

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ)። መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት። በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል። በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም።*

### ድራማ

1. በአብዛኛው በተውኔት ገፀባህርያት የሚተዋወቁበት መንገድ ገፀባህርያቱን ለመረዳት ጠቃሚ ነው። የተለያዩ ፀሀፌ ተውኔቶች ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ገፀባህርያት እንዴትና ለምን እንደተዋወቁ ግለጽ።

2. «በድራማዊ አጻጻፍ ዋናው ጉዳይ ግጭት፣ ግጭት፣ ግጭት ነው።» የተለያዩ ፀሀፌ ተውኔቶች ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ዋነኛዎቹ ግጭቶች የየቀረቡበትን መንገድና ፀሀፌ ተውኔቶቹ ድራማውን ለማጎልበት የተጠቀሙበትን ሁኔታ አስረዳ።

### ረጅም ልቦለድ

3. በረጅም ልቦለድ ስለገፀባህሪቱ በከፊል የምናውቀው ሌሎች ገፀባህርያት ስለነሱ ከሚናገሩት ነው። ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ገፀባህርያት በዚህ መንገድ እንዴት እንደቀረቡ ግለጽ።

4. ማንኛውም ረጅም ልቦለድ ተአማኒ ድርጊትና ማራኪ ገፀባህርያት ሊኖሩት ይገባል። መልስህ ያነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚጠቅስ ይሁን።

### ስነግጥም

5. በግጥም ዘይቤ ጠቃሚ የሚሆነው አንድን ጉዳይ አዲስና ትኩስ አድርጎ ማቅረብ በመቻሉ ነው። ይህንን ሃሳብ ያነበብካቸው የተለያዩ ገጣምያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ግጥሞች በመመርኮዝ ግለጽ።

6. የስነግጥም ዋና መሰረቱ ምስል የሚፈጥሩት ቃላት ናቸው። ባነበብካቸው የተለያዩ ገጣምያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ግጥሞች ውስጥ ገጣሚዎቹ ሃሳብን በሚገባ በመግለጽ ችሎታቸው ያለንበትን ሁኔታ ፍንትው አድርገው ማሳየታቸውን አሳይ።



https://xtremepape.rs/

## ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)

7. ማንኛውም ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) የሚቀርበው ከፀሀፊው የግል አመለካከት አንጻር ነው። ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ የግል አመለካከታቸውን በምን ደረጃ እንደተጠቀሙበት አሳይ።

8. የዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) አቅራቢ ታሪኩን በገለጻና በምልልስ ሊያቀርብ ይችላል። ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ይህ ዘዴ እንደምን ጥቅም ላይ እንደዋለ አስረዳ።

## አጭር ልቦለድ

9. በአጭር ልቦለድ የገጸባህሪው ድርጊት ተአማኒ እንዲሆን ለማድረግ ደራሲው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የገጸባህሪው ባህሪ የተከሰተበትን ምክንያት መግለጽ አለበት። ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ በዚህ መንገድ የገጸባህሪያት ድርጊት ተአማኒ ሆኖ የቀረበበትን መንገድ አስረዳ።

10. የአጭር ልቦለዶች ገፀባህርያት በአብዛኛው የተሳሉበት መቼት ውጤቶች ናቸው። ይህንን ሃሳብ ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት አጭር ልቦለዶች በማወዳደር ግለጽ።

## ሁለገብ (አጠቃላይ)

11. ስነጽሁፍ መልካም ሰዎች መሆን የምንችልበትን አቅጣጫ ሊያሳየን ይችላል። ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር መልስ ስጥ።

12. ስነጽሁፍ ስለሰዎች የእርስበርስ ግንኙነት እንድናውቅ ይረዳናል። ይህንን ሃሳብ ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር አብራራ።

13. የስነጽሁፍ ስራዎች የሚቀርቡት ግንዛቤያችንን ከፍ ለማድረግ እና ስሜታችንን ለመኮርኮር ነው። ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ።

14. የስነጽሁፍ ስራዎች አእምሮአችን ጠቃሚና ማራኪ ሀሳቦች እንዲያውጠነጥን ያደርጋሉ። ይህንን ሃሳብ ባነበብካቸው የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ምሳሌነት አብራራ።



https://xtremepape.rs/